Triki, Touraya, and Faye, Issa. *Financial Inclusion in Africa*. African Development Bank, 2013.

http://fas.imf.org/Default.aspx

Demirguc-Kunt et al.

Hakura et al. **Sustaining More Inclusive Growth in the Republic of Congo**. African Department, IMF, 2015.

http://www.reuters.com/article/2015/04/27/ziraat-ethiopia-idUSL8N0XO2O520150427, April 27, 2015.

Stijn Claessens, Asli Demirgüç-Kunt, and Harry Huizinga. **How does foreign entry affect domestic banking markets?.** World Bank, 2000.

Enrica Detragiache, Poonam Gupta, and Thierry Tressel. **Foreign Banks in Poor Countries: Theory and Evidence.** IMF, 2006.

Triki, Touraya, and Faye, Issa.

Financial Inclusion in Africa. African Development Bank, 2013.

Cont. to page 14

ፓንቶ ማይም የምልክት ቋንቋና ኮሜዲ ያላቸው ተዛማጅነት

እቴነሽ አበበ

ጥንት በግሪክና በሮማ ይዘጋጁ በነበሩ የቴአትር መድረኮች ጭምብል ያደረጉና በሚዚቃና ሕብረ ዝማሬ የታጀቡ የፓንቶማም የሚባሉ ድራማዎች ይቀርቡ እንደነበረ ይተወቃል፡፡

ፓንቶ ማይም ልዩልዩ የሰውነት አካላትን በማንቀሳቀስ የሚቀርብ ትርኢት ነው በሌላ አባባል በንግግር ቋንቋ ፋንታ የአካለት እንቅስቃሴን በመጠቀም መልእክት የማስተላለፍ ዘዴ ነው ::

ፓንቶ ማይም / dump show / የደንቆሮ ትርኢት በሚል መጠርያ ይታወቃል ምክንያቱም ትርኢቱ ባብዛኛው የሚገለፀው በአካለት እንቅስቃሴና የፊት ገፅታን በመጠቀም ስለሆነ ነው፡፡ በ16ኛው ምእት አመት በኮሜዲ ዴላርቴ ጥረት ኢጣልያ ውስጥ ያደገው የኮሜዲ ተውኔት መነሻው የግሪክና የሮማ ፓንቶማይም ቢሆንም በኢምሮቫይዜሽን ድንገቴ ትወና የበለፀገ ነበር ተረተረት እንቆቅልሽ የመሳሰሉ ሥነቃሎችንና የባሕል ገፅታዎችን መነሻ መሠረት አድርጎ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ በሚዋነዩ አስቂኝ ገፀባሕርያትና ሥልጡን ባለሙያዎች ይቀርብ ስለነበረ ተወዳጅነትን አትርፎ ወደ አውሮፓና ሌሎች አገሮች ተስፋፍቶ ለኮሜዲው ቴአትር ዘውግ በመነሻነት እየተጠቀሰ እስከለለንበት ዘመን ሊዘልቅ ችሏል ሞልየርና ካርሎ ጎልዶኒ የመሰሉ ዝነና የኮሜዲፀሓፍትን ሊያፈራ በቅቷል፡፡

ሄርሌኩዊን / harelequinn / የተሰኘው ገፀ ባሕሪ በኮሜድን በበኩሉ ከፍለ ዘመናት ቀደም ሲል ኢጣልያዊው ኮሜዲ ዴላርቴ የፈጠራቸውና ያሳደጋቸው አስቂኝ ገፀ ባሕርያት ባለብዙ ቀለም ቀለም ሰፋፊ ሱሪና ኮት ለየት ያሉ ኮፍያ ወይም ዊግ የተሌ አይነት ጫማ አንዳንዶቹም ጭምብል /ማስክ/ ሊኖራቸው የሚችሉ ገፀባህርያትን በመፍጠር በፈረነረሳይ ና በእንግሊዝ ተረት አፈ ታሪክ ሥርአተ አምልኮ የመሳሰሉ ትውፊቶችን መነሻ ያደረጉ በየአገሮቻቸው ባሕላዊ ገፅታዎች ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ አይነት ፓንቶማይሞች እንዲወጡ አድርጓል፡፡

በ18ኛው ክፍለ ዘመን ጆን ሪች የተባለ የእንግሊዝ ተዋናይ የሃርሊኩን ገጸባሕርት በገና በአል ዋዜማና ለበአሉ እንዲስማማ አድርጎ በመተወን ታላቅ እውቅናን አግኝቷል።



በ19ኛው ክፍለ ዘመን ተወዳጅነትን እያተረፈ የመጣውንና ገና ከመነሳው የፊት ገፅታን የእጅና የእግር እንቅስቃሴን በመጠቀም በቃል ከሚቀርብ የንግግር ድራማ ውጭ የሚሰራውን /ወጥ የሆነ ዲያሎግ ልነበረው / የድራማ አይነት በአልባሳት በገፅቅብ በሙዚቃ በአክሮባትና በመጠነኛ ቃለ ምልልስ የምትሐት ትርኢት በማካተትና የመድረክ አጠቃቀም ዘዴዎችን በማሳደግ የእንግሊዙ ጆሴፍ ጊርማልዲ የሞኝ መልክ በያዘና / clown / ጆይን በመሰኘት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቀውን ገፀባሕሪ ሊፈጥር ችሏል፡፡

የታወቀው የጌር ማልዲ ክላውን ጆይ በፓንቶ ማይም ከፍተኛ ችሎታ የነበረው ፈረንሳይ ጂን ጋርፖር ዲቦራ በኮሜዲያ ዴላርቴ የተቀረፀውን በፍቅረኛው ባለመፈቀሩ ሃዘንና ብቸኝነት ጠቃውን አፍቃሪ የወከለውን ገፀ ባህሪ በአልባሳት በገፅ ቅብና በአክሮባት እንዲያሸበርቅ በማድረግ ወደ ተወሳሳበ ባህሪ ማሻጋገር የቻለ ዘዴኛ ነው፡፡ /ethiene decrown marecel marceau/ ፓንቶ ማይም ከፍተና ችሎታን ክህሎትንና ስልጠናን የሚጠይቅ አይነት ድራማ መሆኑን ፈረንሳይ ውስጥ ያሳዩና ያስገነዘቡ ናቸው ::በተሌ ማርሴ ማርከ // በነጭ የፊት የገፅ ቅብ የተቀባና የተለየ ጫማና ባርኔጣ ወጣትነት ጎልማሳነት እርጅናን ሞትን ሙሉ ታሪከና ሴራ ኖሮት በአንድ ሰው ብቻ በተከታታ በማይም ቴአትር አማካይነት የሚቀርብበትን መንገድ ቀየሰ 20ኛው ክፍለ ዘመን ጥበብ ነው፡፡

የፓንቶ ማም አቀራረብን በመጠቀም የቻርሊ ቻፕሊን ድምፅአልባ የፊልም ጥበብም እንዲፈጠር ያስቻለ ሰው ነው፡፤

የእንግሊዙ ቻርሊ ቻፕሊን ቀደም ሲል በጣልያን በፊረንሳይ በእንግሊዝ እያደገ የመጣውን የፓንቶ ማይም ድራማ ገፀ ባህሪ በመውረስ ከራሱ አካላዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ለራሱ በሚስማማና ይበልጥ ገላጭነት ባላቸው አልባሳት ጫማ ቁሳቁስ የገፅ ቅብ በማሸብረቅ ከሁሉም የጥበብ ዘርፎች በተውጣጣ የአተዋወን ክህሎት ፤ብቃትና ዘዴ በማጠናከር በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ለራሱ በሚመቸውና በበለተ ገላጭ በሆነ ዘዴ በማጠናከር ፓንቶ ማይምን በታሪኩ የዳበረ መልክ እንዲጎናጸፍ በማድረግ ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋግሮታል :: ጊዜው የፊል ም ጥበብ ያቆጠቆጠበት ስለነበረ ፊልሞችን በንግግርና ዲያሎግ መስራት እስከ ተቻለበት ወቅት ድረስ የድምፅ አልባው ፊልም ሥራ የቻርሊ ቻፕሊ ፓንቶ ማም አተዋወን ዘዴ ውጤት የሆነውን የፊልም ጥበብ ባለሃብት እንድንሆን አስችሎናል :: በሌላ በኩል በፓንቶ ማይም የታሪክ ጉዞ የጃፓኑ /no/ እና /mad words/ የጀርመኑ /faust/ የ ሕንዱ /Sanskrit , kathakali/ እና ሌሎችም እዚህ ያልተጠቀሱ ድራማዎች በየአገሮቹ ባሕል መነሻነት የተሰሩት በዘመናችን የቴአትር ጥበብ ለደረሰበት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማበርከት የሚጠቀሱ ናቸው ::

ፓንቶ ማይምና የምልክት ቋንቋ

ሁለቱም መሠረት የሚያደርጉት ባሕል ፤ ተረት ፤ ሥነቃል ፤ ትውፊት ፤ ስርዓተ ኣምልኮ እንደ ፈተታቸው ይጠቀምቡታል፤

የፊት ገፅታንና የሰውነት አካላዊ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ይጠቀማሉ፤

ፓንቶ ማይም ለመዝናናት ለማስተማር የሚጠቅም የትርኢት ዘርፍ ነው፤

የምልክት ቋንቋ መሥማት የተሳናቸው ሰዎች የንግግር ቋንቋን ተክተው የምግባቡት ዘዴ ነው፡፡

የምልክት ቋንቋ መስማት የተሳናቸው ወገኖች በልዩ ልዩ አካላዊ እንቅስቃሴ ሃሳባቸውን በመግለጽ ከሌሎች ጋር ,የሚግባቡት ዘዴ ነው :: የመግባቢያ ዘዴው ሁሌም የሚነሳውና መሠረት የሚያደርገው የመነጨበትን ማሕበረሰብ ባሕል በመሆኑ መግባቢያው የሚገለፅበት ምልክት ከዚያው ስለሚወጣ አባላቱን እርስ በርስ ለመግባበት ያስችላቸዋል እንደገናም የየአካባቢቸውን ቀበልኛ እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል :: ከዚህም በላይ የምልክት ቋንቋ የፊት ገፅታን ፤ እጅንና የሰውነት አካለትን በማንቀሳቀስ የሚገለፅ ፤ የመገንዘብና የመረዳት ስነልቦናዊ ፍላጎት የመቀስቀስ ሃይል ስለሚታይበት የተዋንያንን ክህሎት ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

ፓንቶ ማይምና የምልክት ቋንቋ በኮሜዲ ዘውግ ውስጥ ስላላቸው ተወራራሽነት በጥቅሉ ሲታይ በዘውግ አፈታቱ አስቂኝ አጨራረስ ያለው ድራማ በታሪኩና በሴራው ከኮሜዲ ቢለይም የፓንቶማይም እንቅስቃሴ በተዋናዩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው ::

የቴአትር ስራ ወደ አገራችን የገባው ከዘመናዊ ትምሕርት ጋር ተያይዞ በመሆኑ ለኢትዮጵያ አዲስ ባህል ነው :: ይህም አዲስ ባሕል በመጀመር የተቀበሉት ዮፍታሔ ንጉሴና መላኩ በንሰው ናቸው :: እነዮፍታሄ በ"አፋጀሽኝ" አማካኝነት የጀመሩት ኢትዮጵያዊኛ ቴአትር ? መነሻ መሠረቱ ተረታችን ቢሆንም እንደ አጀማማሩ አላደገም :: በመሆኑም እንደ ሌሎቹ አገሮች የራሳችን የሆነ መጠርያ አልፈጠርንም ይኸ በጥቅሉ የምናየው እውነት ነው::

በፓንቶ ማይም ድራማ በኩል ስንመለከት የአውሮፓውያን የገፅ ቅብና አልባሳት የተጠቀሙ አርቲስቶች ፎቶግራፍ / ተስፋዬ ሳህሉና በላይ መረሳ / ማግኘት ቢቻልም ለመድረክ አስተዋዋቂነት እንደለበሱት ነው የሚታወቀው ታዋቂው ተዋና ወጋየሁ ንጋቱ በ1970 ዎቹ በኢቲዮጵያ ብሔራዊ ቴአትረ በሚዘጋጀው ልዩ ትእይንት ጥበባት ፕሮግራም ላይ የተለያዩ ፓንቶማይሞችን ያቀርብ ነበር ከነዚህመ ውስጥ "ባሉኑ ፤ ቁንጫው " የተሰኙ ፓንቶ ማይሞች ይቀር ቡ ነበር ትርኢቶቹ በራሳቸው ምሉዕ የነበሩና በከፍተኛ የመዋነይ ክህሎት የቀረቡና የማርሴይን ገጽ ቅብና አልባሳት አቀራረብ የተከተሉ እንደነበሩ ታውቋል፡፡

እስታንደ አፕ ኮሜዲ /standup comedy/

እነዚህ ከአስተዋዋቂነት ትንሽ ከፍ የሚሉና በፓንቶማይምነት ደረጃ ሲታዩ ባዶ ሆነው የሚገኙ የተመለደ አይነት የመዋነይ ዘዴ ሆኗል :: የዚህ አይነቱ እስታንዳፕ ኮሜዲ በአውሮፓና አሜሪካ ... ለሌላውም አለም እየተሰራበት ያለ ድራማ ነው :: ድራማው በአብዛኛው የተናጋሪ ፤ የዲስኩረኛ ፤፤የማስመሰልና ፤ የማሸሚጠጥ ባሕሪያትንና በጣም ባልተንዛዛ ሁኔታ መዋነይን የሚጠይቅ ድራማ አይነት ነው ::

ስሙ እንደሚያመለክተው አንድ ቦታ ተቁሞ የሚሰራ መሆኑን ተገንዘቡልኝ ፤ባብዛኛው እስታንዳፕ አፕ ኮሜዲ ለሴቶች መብት ተሟጋቾች /feminist movement, green movement / በከፍተኛ ደረጃም ለቅስቀሳና ለማስተማርያ የሚጠቀሙበት ፤በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ የፖለቲካ ውዝግቦችም የሚሄስበት ነው:: ተዋናዩ ለሚመርጠውና ለሚያቀርበው ትርኢት አመቺ ይሆናል የሚለውን አልባሳት ይጠቀማል ፤ገፅቅበና ሌሎች ተዛማጅ ነገሮችን የመጠቀም ግዴታ የለበትም ፤ተዋናዩ ድምፅን በመቀያየር ላይ የተመሰረተ የአተዋወን ብቃት ነው ባብዛኛው የሚጠበቅበት ::

ማጠቃላያ

ፓንቶ ማይምና የምልክት ቋንቋ ኮሜዲ በኢትዮጵ ቴአትር ታሪክ ምን ቦታ አላቸው ? ፓንቶማይም ሆነ የምልክት ቋንቋ አሁን "ኮሜዲ" እያልን ለምናቀርባቸው ትርኢቶች ያላቸው አስተዋፅአ ምንድነው? በርግጠኝነትስ "ኮሜዲ" ወይም "ፓንቶ ማይም" የምንለው አይነት ትርኢት አለን ወይ ? የ "ከሜዲ" ፓንቶ ማይሞች ተዋናዮች የመዋነይ ክህሎት ፤ አልባሳትና የገፅ ቅብ አጠቃቀማቸው ፤የእጅና እግር እንቅስቃሴአቸው .... ወዘተ ... ብቃት ምን ያህል የዳበረ ነው ? .... ወዘተ ... የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀሬ ነው .... የዚህ ፅሁፍ አላማ በነዚህ ነገሮች ላይ ግምገማ ማካሄድ ሳይሆን ከሰማንያ አምስት ብሔር ብሔረሰቦች በላይ አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ የሚገኙት የዘልማድ የምልክት ቋንቋዎች እየተጠኑ ቢመዘገቡ ፤ለወደፊቱ የፓንቶማይም "ኮሜዲ " ትርኢቶች መሠረቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመጠቆም ነው ፤ የምልክት ቋንቋ ተናጋሪ ማሕበረሰብም በባሕሉ ላይ የተመሠረተ የዳበረ ምሉዕ የሆነ አረፍተ ነገር ያገኛልና ፤ የባሕል አጥኝዎችም የየብሔረሰቡ የመግባቢያ ምልክቶች በግሎባላይዜሽን ማዕበል እየሰመጡ ጠፍተው ከመረሳታቸው በፊት ጥናት እንዲካሄድባቸውና የኢትዮጵያዊኛ ቴአትር መሠረት እንዲሆኑ ለማሳሰብ ነው ::

እቴነሽ አበበ heelafam@gmail.com አስተያየት መላክ ትችላላችሁ

በእምነቱ የኖረ

ያደለበዉን ከብት፡
ለእምነቱ ብሎት፡
ትግስቱ በዝቶለት፡
እንደ እዮብ ሆኖለት፡
ያሳደገዉን ላም አኑርዋት በበረት፡
ፍሩሽካና ሳሩን በአግባቡ ሰጥቶ፡
ከብቱ ሲያምርበት ፈተና መጣበት፡
ችግርና ረሀብ ተፈራረቁበት፡
ፀሎትና ጾሙን በርትቶ ገፋበት፡
እምነቱን ከሚሸር በእምነቱ ሞተበት፡
ሚስቱን ልጁን ዘሩን ሁሉ ቢያጣበት፡
እንደ እዮብ ትግስት እምነቱን ካበበት፡፡
ከ ሶስና ገብረስላሴ

Financial. . . Cont. from Page 14



Source: IMF Financial Access Survey Database.

Ethiopia

Sub-Saharan Africa			Low income
Population, age 15+ (millions)	53.9	GNI per capita ($)	470

	Country data	Sub-Saharan Africa	Low income
Account (% age 15+)			
All adults	21.8	34.2	27.5
Women	21.0	29.9	23.9
Adults belonging to the poorest 40%	15.9	24.6	19.4
Young adults (% ages 15–24)	14.3	25.9	20.2
Adults living in rural areas	18.7	29.2	24.8
Financial Institution Account (% age 15+)			
All adults	21.8	28.9	22.3
All adults, 2011	..	23.9	21.1
Mobile Account (% age 15+)			
All adults	0.0	11.5	10.0
Access to Financial Institution Account (% age 15+)			
Has debit card	0.8	17.9	6.6
Has debit card, 2011	..	15.0	6.3
ATM is the main mode of withdrawal (% with an account)	0.9	53.8	20.2
ATM is the main mode of withdrawal (% with an account), 2011	..	51.7	19.7
Use of Account in the Past Year (% age 15+)			
Used an account to receive wages	0.7	7.3	3.2
Used an account to receive government transfers	0.3	3.8	1.0
Used a financial institution account to pay utility bills	0.1	2.8	0.9
Other Digital Payments in the Past Year (% age 15+)			
Used a debit card to make payments	0.0	8.7	2.1
Used a credit card to make payments	0.2	1.9	0.6
Used the Internet to pay bills or make purchases	0.4	2.4	1.2
Domestic Remittances in the Past Year (% age 15+)			
Sent remittances	9.9	28.7	18.3
Sent remittances via a financial institution (% senders)	..	31.0	15.4
Sent remittances via a mobile phone (% senders)	..	30.8	42.8
Sent remittances via a money transfer operator (% senders)	..	21.0	14.1
Received remittances	8.6	37.2	25.6
Received remittances via a financial institution (% recipients)	..	26.6	13.0
Received remittances via a mobile phone (% recipients)	..	27.6	33.8
Received remittances via a money transfer operator (% recipients)	..	22.1	14.8
Savings in the Past Year (% age 15+)			
Saved at a financial institution	13.6	15.9	9.9
Saved at a financial institution, 2011	..	14.3	11.5
Saved using a savings club or person outside the family	29.8	23.9	16.3
Saved any money	48.1	59.6	46.5
Saved for old age	8.0	9.8	8.3
Saved for a farm or business	14.9	22.7	16.7
Saved for education or school fees	8.3	22.9	16.6
Credit in the Past Year (% age 15+)			
Borrowed from a financial institution	7.4	6.3	8.6
Borrowed from a financial institution, 2011	..	4.8	11.7
Borrowed from family or friends	29.5	41.9	34.9
Borrowed from a private informal lender	1.1	4.7	6.5
Borrowed any money	43.5	54.5	52.5
Borrowed for a farm or business	11.5	12.8	12.2
Borrowed for education or school fees	4.2	12.3	10.9
Outstanding mortgage at a financial institution	2.0	5.2	4.1

Source: World Bank, Findex Database.

My Sweet Slavery

I don't know if u like me or not
But whenever u want, I give what I got
U call me per day or two
I answered double than u
U see me whenever u want
I am there by any chance I get
U tell me that u like me tonight
Tomorrow u act like u forgot
U said u r sorry for not calling back
But still u didn't make up for that
For whatever u do I cover for u
Let alone the reality, let alone the truth
Though u hurt me hard
Though u beat me hard
I will be there when u r so sad
Though the people say u r badly for me
Though the people say we r not mean to be
All I know that u r my burden, my job
My sweet slavery.

Haimanot Aserat

Keep on Keeping

I keep of falling
Falling for my mistakes.
Causing me a lot of heart breaks
I keep on denying
Denying about my habits
Causing me a lot of damages.
Keeping on falling, keep on denying
I lost my faith, I also lost my trying
Sharing the burden is like a must
But sharing the good is very difficult.
I keep on loosing
Loosing all the games
Causing a lot of head downs.
I keep on hiding
Hiding from the truths
Causing me loose all my virtues.
Keeping on loosing, keeping on hiding
I lost my spirit, I also lost my beating
But keeping my value is very difficult
To be a looser doesn't seem very hard.
Though I keep on falling
Though I keep on loosing
I will keep on keeping my promise for surviving!!

Haimanot Aserat

Community Page

Ethiopian Community Center in Maryland (ECCM)

Montgomery College Open house for the Ethiopian Community in partnership with ECCM

Incorporation

It has been established and incorporated in the State of Maryland in January, 2013.

Objectives

To provide reliable, quality, and accessible community services to all in Maryland, regardless of age, sex, or other social, economic or ideological differences; with the goal of promoting self-sufficiency, cultural enrichment, and understanding and appreciation of Ethiopian culture and history. ECCM will also serve as a center for safety and emergency response during accidents or during urgent need of community members.

Organization

Board of Directors, executive directors (President, Vice President, Secretary, Treasurer, finance officer & Public relations) two staffs one as a senior project coordinator and one as a project coordinator. ECCM has tentatively formed seven committees to facilitate achieving its short term and long term objectives. These committees have been formed based on needs assessment and ECCM expects strong support from the community to make these programs successful. Currently, Board of Directors have 14 members whom are founding members of ECCM. There is a plan to start membership accordingly, future board of directors will be elected by the general assembly.

ECCM Funding

Community Development Block & Council grants from Montgomery County and fundraisings.

ECCM Services

Because of limited resources ECCM has identified programs that can start immediately and programs that will start in the short term and programs that will start in the long term. ECCM will leverage its resources by forming close partnership with schools, government agencies, employment agencies and healthcare providers. Program focus areas includes; Health, Education, Job, Immigration, Legal issues and others. ECCM currently making efforts in positive youth development and health programs. ECCM has been organizing and mobilizing health service providers to volunteer for community health screening, testing and counseling services and provide several information of service givers in Maryland particularly in Montgomery County. To mention some of the exemplary projects; The soccer clinic program summer 2014 for 42 kids in collaboration with Washington Adventist University.

December, 2014 – February, 2015 Affordable care Act Insurance enrollment out reach for thousands of Ethiopians in Maryland in collaboration with Montgomery county Department of Health and Human Services. A number of health fairs and workshops at Dc Mariam Church, 3 selected apartments at Takoma park MD. May, 2015

Education open house for the Ethiopian Community in collaboration with Montgomery College more than 300 people attended the event

ECCM health workshop for Seniors at Victory towers apartment (presenter form The Peson's Center, Mrs. Amilia Missieledies)

Membership

Membership have not started yet, all who live in Maryland particularly Ethiopians will get the service whether they are a member or not.

Customers

All who live in Maryland get the service through health care projects and the Affordable Care Act various events, health fares, workshops, Open houses, Apartments, flyers, walk in services at ECCM office Also collaborating with similar organizations, networks, schools, churches& Mosques.

Advertisement

Through the services we provide, free Health fares, different community related events, Open houses, Flyers &Media.

Assessing the Service

We conducted an assessment on the pressing issues among the community before we launched our projects. The assessments were conducted through focus group discussions with college students, women, young professionals, and senior professionals.

We prioritized from the mentioned gaps as the most pressing in the community health and education. We are trying to be transparent and engage the community throughout the activities in order to meet their expectations.

Other Community Centers

There is no established working relationship with other Ethiopian Community centers as of now however, it is in plan for the future.

Majority of the centers have been around here for more than 30 years and have an enormous experience in the area. ECCM is relatively new and still learning from the process and making efforts to design sustainable community based programs.

We are trying to introduce ECCM to other community members there are ongoing efforts to collaborate with other community centers.

ECCM soccer clinic program in collaboration with Washington Adventist University (volunteer coach , Mr. Samuel Estifanos)

For all Your Comments
ለአስተያየታቹህ
Email info@adulis.net
Tel : (301) 565 4910

Disclaimer

Each Author is responsible for his/ her own article. Adulis does not necessarily share the contents of the articles.

የትግል ስትራቴጂ ምንነት እና የትግል ስትራቴጂ መረጣ
ታደሰ ብሩ

በዚህ ጽሁፍ ስለትግል ስትራቴጂ ምንነት እና ስለስትራቴጂ መረጣ አንዳንድ ሀሳቦችን ለማቅረብ እሞክራለሁ። የኔ ትኩረት የፓለቲካ ስትራቴጂዎች ላይ ሆነ እንጂ እዚህ ላይ የሰፈሩ ሀሳቦች ቢዝነስን ጨምሮ ማናቸውም ዓይነት ሁነኛ ዓላማ ለማሳካት በሚደረግ የስትራቴጂያዊ ፕላን ጥናት ውስጥ አገልግሎት ውስጥ ሊውሉ የሚችሉ ናቸው።

ይህ ፅሁፍ ሶስት ክፍሎች አሉት። ክፍል አንድ የትግል ስትራቴጂ ምንነት ላይ ሲያተኩር ክፍል ሁለት ደግሞ ስለስትራቴጂ ማኔጅመንት አጭር ገለፃ ይሰጣል። እነዚህ ሁለቱ ክፍሎች ከእኔ የግል የፓለቲካ እምነት ነፃ ናቸው። ይህም ማለት እንደ ማኔጅመንት ትምህርት አካል ሊወሰዱ ይችላሉ። ክፍል ሶስት ለአገራችን ይበጃታል ብዬ የማምነውን የትግል ስትራቴጂ ለኔ በገባኝ መጠን ለማብራራት እሞክራለሁ። ይህ ክፍል በኔ የፓለቲካ እምነት የተቃኘ በመሆኑ ሀሳቤን የሚደግፉም ሆነ የሚቃወሙ ሊኖሩ ይችላሉ። የዚህ ሀሳብ ደጋፊዎችም ሆነ ተቃዋሚዎች የሚያቀርቡትን ሥርዓት የተከተለ ክርክር በጥሞና ለማዳመጥ ዝግጁ ነኝ።

የትግል ስትራቴጂ ምን ማለት ነው?

"ስትራቴጂ"፣ አንድ ድርጅት ተልዕኮውን ለማሳካት የሚወስዳቸው ተከታታይ ተግባራትን የሚያመላክት ጥቅል መመሪያ ነው። ተልዕኮ ማለት ደግሞ አንድ ድርጅት የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ ማለት ነው። ስለሆነም ስትራቴጂ አንድ ድርጅት የተቋቋመበትን ዓላማ እንዴት እንደሚያሳካ የሚገልጽበት መንገድ ነው። የፓለቲካ ስትራቴጂ የፓለቲካ ግብ እንዴት ለማሳካት እንደታቀደ በጥቅሉ የሚገለጽበት አቅጣጫ ጠቋሚ ነው። የፓለቲካ ስትራቴጂ በመሠረቱ የትግል ስትራቴጂ ነው።

የትግል ስትራቴጂ ለመንደፍ፣ በቅድሚያ ስትራቴጂው እንዲያሳካቸው የሚፈለጉ የፓለቲካ ግቦች በግልጽ ሊታወቁ ይገባል። አምባገነን ሥርዓትን መጣል አንድ የፓለቲካ ግብ ሊሆን ይችላል። በወደቀው ሥርዓት ምትክ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ደግሞ ተከትሎ የሚመጣ ሌላ ግብ ሊሆን ይችላል። በዚህ አይነት ግቦችን ዋና እና መለስተኛ እያልን ደረጃ ልናወጣላቸው፤ ቀዳሚ እና ተከታይ እያልን ቅደም ተከተል ልናበጅላቸው እንችላለን። ከዚያም እያንዳንዱን ግብ ለማሳካት ምን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ማጤን ሲጀመር የትግል ስትራቴጂ ጥናት ተጀመረ ማለት ነው። የስትራቴጂ ጥናት የአንድ ወቅት ሥራ አይደለም፤ ስትራቴጂያዊ እቅድም አንዴ ተሰርቶ ለማጣቀሻነት የሚቀመጥ ጥራዝ አይደለም፤ ሁለቱም እታለመው ግብ እስኪደረስ ድረስ የሚቀጥሉ የዘወትር ተግባራት ናቸው።

የትግል ስትራቴጂ አሁን ያሉትን ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል የሚባሉ ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶችን (ችግሮችን) ታሳቢ ያደረገ እና አቅምን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል። ስትራቴጂ ግብን ለማሳካት በተግባር ላይ መዋል ያለባቸው ስልቶች፤ እነዚህ ስልቶች የሚጠይቁት ግብዓት፣ ድካምና የመስዋዕትነት መጠን ያመላክታል።

የሚከተሉት ጥያቄዎች ለፓለቲካ ስትራቴጂ ጥናት ወሳኝ ናቸው።

1. ምንድነው የምንፈልገው? የምንታገለው ምን ለማግኘት ነው? ወይም በተለመደ አነጋገር "የት መድረስ እንፈልጋለን?"
2. የምንፈልገውን ለማግኘት ምንድነው ማድረግ ያለብን? በተለመደው አገላለጽ "ምን ዓይነት አማራጭ መንገዶች አሉን?"
3. እያንዳንዱ አማራጭ ምን ዓይነት ግብዓቶች ይጠይቃል? ምን ዓይነት ሰው? ምን ያህል ሰው? ምን ዓይነት ችሎታዎች? እንደምን ያለ አደረጃጀት? ምን ዓይነት አመራር? እንደምን ያለ ቴክኖሎጂ? ምን ዓይነት ቁሳቁስ? ምን ያህል ገንዘብ? ፣
4. ውጫዊ ሁኔታዎች ምን ያህል የተመቻቹ ናቸው? ውጫዊ ሁኔታ ሲባል ከድርጅቱ ውጭ ያለው ፓለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የተፈጥሮ፣ የህግና የቴክኖሎጂ ሁኔታዎችን ሁሉ ያጠቃልላል።
5. ውስጣዊ ሁኔታዎች ምን ያህል የተመቻቹ ናቸው ? ውስጣዊ ሁኔታ ሲባል የአባላትና ደጋፊዎች ብዛትና ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ያላቸው ዝግጁነት፣ ድርጅታዊ ዲሲፕሊን፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ እውቀትና ክህሎት፣ መረጃና እና ቁሳቁስ ያጠቃልላል።
6. የትግሉ ባለቤቶች (ግንባር ቀደም መሪዎች) እነማን ናቸው? የትግሉ ደጋፊዎች እነማን ናቸው? ባለድርሻ አባላት እነማን ናቸው? ድርሻቸው ምን ያህል ነው? አዎንታዊ ወይስ አሉታዊ?
7. ጠላት ወይም ተቀናቃኝ ማነው? የተቀናቃኞቸን ጥንካሬዎቹ ምንድናቸው? ድክመቶቹስ ?

የስትራቴጂ ጉዳዮች (strategic issues)

የድርጅት ስትራቴጂ ከድርጅት ተልዕኮ ጋር በቀጥታ የተገናኘ መሆኑ ከላይ ተጠቅሷል። የድርጅቱን ተልዕኮ ስኬትና ውድቀት የሚወስኑ ጉዳዮች "ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች" ናቸው። በስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትክክለኛ ውሳኔ ተሰጥቶ ተግባራዊ ከተደረገ ድርጅቱን ወደ ስኬት ያቀርቡታል። በስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ስህተት ከተፈፀመ ደግሞ ድርጅቱን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላሉ። የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ናቸው።

1. የትግል ስትራቴጂዎችና ስልቶች ምርጫ
2. አመራርና ውስጣዊ አደረጃጀት
3. የአጋር መረጣ - ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ውህደት፣ ጥምረት፣ እና ትብብር

የግብዓቶች ዓይነቶች እና ስምሪት - አባላት፣ የአባላት አስተዳደር፣ ንብረት፣ የንብረት አስተዳደር

የስትራቴጂ ደረጃዎች

ግቦች የተለያየ ደረጃ እንዳላቸው ሁሉ ስትራተጂዎችም ደረጃቸው ይለያያል።



ስዕል 1: የስትራቴጂ ደረጃዎች

ከላይ በስዕል ፡ እንደተመለከተው የድርጅቱን ተልዕኮ እና ዋና ዋና ግቦችን ለማሳካት የሚወጣው ስትራቴጂ የድርጅቱ አቢይ ስትራቴጂ ነው። አቢይ ስትራቴጂ በአንፃራዊ መልኩ ቋሚና የረዥም ጊዜ እይታን ይዞ የሚነሳ ነው።

በየጊዜው የሚፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም እና/ወይም በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮች የሚያመጡትን ጉዳት በመቀነስ ጠላትን ማዳከም፤ ከሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች በልጦ በመገኘት ወይም ይዞታ በማስፋት ላይ ያለሙ ስትራቴጂዎች መለስተኛ ስትራቴጂዎች ወይም የታክቲክ ስትራቴጂዎች ይሰኛሉ። ዋናው ዓላማቸውም ምቹ ሁኔታዎችን መጠቀም (ወይም ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎችን በጥበብ ማለፍ) በመሆኑ መለስተኛ ስትራቴጂዎች ከሁኔታዎች መቀየር ጋር መቀየር አለባቸው።

በመጨረሻም በትግበራ ላይ ያሉ ሥራዎች የሚመሩበት መርህ የዘመቻ ወይም የትግበራ ስትራቴጂ(Operational strategy) እንለዋለን። የትግበራ ስትራቴጂ የሰው፣ የንብረት፣ የመረጃ ማኔጅመንትን ይመለከታል።

የስትራቴጂ ማኔጅመንት ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች

የስትራቴጂ ማኔጅመንት ከዚህ በታች በስዕል 2 የተመለከቱ ሶስቱ ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። እነዚህም የስትራቴጂ ጥናት፣ የስትራቴጂ ምርጫ እና የስትራቴጂ ትግበራ የሚባሉት ናቸው።



ስዕል 2: የስትራቴጂ ማኔጅመንት ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች

የስትራቴጂ ጥናት

የስትራቴጂ ጥናት የጠላትንና የራስን አቅም በመፈተሽ ያሉትን አማራጭ ስትራቴጂዎችን የመፈለግ ሥራ ነው። ለስትራቴጂ ጥናት የሚረዱ በርካታ የምርምር ሞዴሎች አሉ። ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ለአብነት ያህል ቀርበዋል።

የአካባቢ ጥናት (Environmental Analysis) – ይህ

የአገሪቱን የፓለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የቴክኖሎጂ፣ የህግና የታሪክ ጉዳዮችን በመተንተን ዓላማችንን ሊያሳኩ የሚችሉ ምን ዓይነት የስትራቴጂ አማራጮች ይኖራሉ ብሎ የሚጠይቅ ጥናት ነው።

⇒ ጥንካሬና ድክመት ፍተሻ (SWOT Analysis) - ይህ የራስን ጥንካሬና ድክመት ከአካባቢው መመቸትና አለመመቸት ጋር በማዛመድ የሚደረግ ጥናት ነው።

⇒ "የቢሆንስ" ጥናት (Scenario Analysis) - እንዲህ ቢደረግ ምን ይከተላል፤ እንዲህ ቢሆንስ? ከዚያስ? እያለ ምክንያቶችንና ውጤቶችን እያቀጣጠለ የወደፊቱን ለመተንበይ የሚጥር ጥናት ነው።

⇒ የተወዳዳሪነት ጥናት (Competition Analysis) - ራስን ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ድርጅቶች ጋር በማወዳደር በልጦ ለመገኘትና ለብቻ ለማሸነፍ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ለመፈለግ የሚውል ዘዴ 10.5

የስትራቴጂ ምርጫ

ከላይ በተመለከተው መንገድ ጥናት ተደርጎ የስትራቴጂ አማራጮች ከመጡ በኋላ የድርጅት መሪዎችን ወይም ፓለቲከኞችን የሚጠቅቸው ትልቁ ሥራ ከቀረቡት አማራጭ ስትራቴጂዎች መካከል የተሻለውን መምረጥ ነው። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ግለሰቦችም አጣብቂኝ ውስጥ የሚገቡት እዚህ ደረጃ ላይ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የፓለቲካ ስትራቴጂ አማራጮች ውስን

የትግል ስትራተጂ .....ወደ ገጽ 18 ዞሯል

በመሆናቸው የስትራቴጂ ጥናት ይደረግ አይደረግ ለብዙ ሰው ግድ አይሰጠውም። የስትራቴጂ ምርጫ ግን እንዲህ በዋዛ የሚታለፍ ነገር አይደለም።

ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ህወሓትን ከስልጣን ለማስወገድ እና በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ የሰፈነበት ሥርዓት ለመገንባት ከሚከተሉት ስትራቴጂዎች የትኛው ተመራጭ ነው?

ሀ) ሰላማዊና ህጋዊ ትግል

ለ) ሰላማዊ ሆኖም ግን ህገወጥ ትግል

ሐ) ትጥቅ ትግል፣

መ) ትጥቅ ትግል እና ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ተቀላቅሎ፣ ወይስ

ሠ) ትጥቅ ትግል እና ሰላማዊና ሆኖም ግን ህገወጥ ትግል ተቀላቅሎ

የሚል ጥያቄ ቢቀርብ የሚሰጠው ምላሽ የሚያስከትለው ውጤት አንድምታ ከፍተኛ እንደሆነ ለብዙዎች የሚያጠራጥር አይደለም። ለዚህ ጥያቄ በቀጥታ መልስ ይስጡም አይስጡም በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ የገቡ የፓለቲካ ድርጅቶች እና ፓለቲከኞች ብቻ ሳይሆኑ ፓለቲካ በቀጥታ አያገባንም የሚሉ የሲቪክ ማኅበራትና ግለሰቦችም ጭምር ከዚህ ጥያቄ ጋር መፋጠጣቸው አይቀርም።

የትኛው የትግል ስትራቴጂ ይበጀናል? ለምን?

በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ የፓለቲካ ፓርቲዎች ከታወቁበት 1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የፓለቲካ ፓርቲዎችን ካወዛገቡ ትላልቅ ርዕሶች አንዱ የትግል ስትራቴጂና ስልት ምርጫ ነው። ለምሳሌ ትጥቅ ትግልን እንደ ስትራቴጂ በመውሰድ ላይ ተስማምተው እያለ "የከተማ ትጥቅ ትግል" ወይስ "የገጠር ትጥቅ ትግል" በሚል የስልት ልዩነት የተፋለሱ፣ ከዚያም አልፎ የተገዳደሉ ድርጅቶችና ስብስቦች መኖራቸው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ዛሬም ፓለቲካችን ውስብስብ ችግር ውስጥ ካስገቡት ጉዳዮች አንዱ ወያኔን በማስወገድ አስፈላጊነት ላይ የሚስማሙ ድርጅቶች በስትራቴጂና በስልቶች ላይ ስምምነት የሌላቸው መሆኑ ነው።

የስትራቴጂ ምርጫ በንድፈ ሀሳብም በተግባርም ውስብስብ ሂደት ይጠይቃል። ከሁሉ አስቀድሞ በአማራጮቹ ዝርዝር ላይ መስማማት ያስፈልጋል። ቀጥሎ ደግሞ መመዘኛዎችን ማውጣትና በመመዘኛዎች ላይ መስማማት ያስፈልጋል። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በመመዘኛዎቹ አለካክ (methodology) ላይ መስማማት ይጠይቃል። በመጨረሻም በውሳኔ ህግ (decision rule) ላይ መስማማት ይጠይቃል።

ነገሩን ለማሳጠር በአማራጭ ስትራቴጂዎች ዝርዝር ተስማማን እንበልና ከቀረቡት አማራጭ ስትራቴጂዎች የተሻለውን በምን መመዘኛ ነው የምንመርጠው ብለን እንጠይቅ። ለስትራቴጂ መረጣ ብዙ መመዘኛዎችን መዘርዘር ብንችልም በሶስት ዋና ዋና መመዘኛዎች ማጠቃለል ይቻላል። እነዚህም

1ኛ) ተስማሚነት (Suitability)፣ 2ኛ) ተፈፃሚነት (Feasibility)፣ እና 3ኛ) ተቀባይነት (Acceptability) ናቸው።

ተስማሚነትን በተመለከተ ቁልፍ ጥያቄ መሆን ያለበት "በአማራጭነት የቀረበው ስትራቴጂ እተፈለገው ግብ ያደርሳል ወይስ አያደርስም?" የሚለው ጥያቄ ነው። የዚህ ጥያቄ መልስ አሉታዊ ከሆነ አማራጭ ተብሎ የቀረበው ስትራቴጂ እውነተኛ አማራጭ አይደለም ማለት ስለሚሆን በዝርዝሩ መውጣት አለበት። ለአሉታዊ ውሳኔ አለመቸኮል ግን ብልህነት ነው። ትንሽም እንኳን እድል ካለው በምርጫው ውስጥ ቆይቶ የሚከተሉት ጥያቄዎች መመለስ ይኖርበታል። ይህ ስትራቴጂ እኛ አገር ውስጥ ይሠራል ወይ? ግልጽ ነው ወይ? ለባህላችን፣ ለአኗኗራችን ተስማሚ ነው ወይ?

ተፈፃሚነትን በተመለከተ መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄዎች የሚከተሉትን የመሰሉ ናቸው። ለስትራቴጂው የሚያስፈልገውን ግብዓት ማግኘት ይቻላል ወይ? ለምሳሌ ስትራቴጂው የሰለጠኑ ሰዎችን የሚፈልግ ከሆነ እነሱን ማግኘት ይቻላል ወይ? በርካታ ሰው በአንዴ "ሆ" ብሎ መነሳት የሚኖርበት ከሆነ ይህንን ማምጣት ይቻላል ወይ? ስትራቴጂው የሚፈልገው ድርጅታዊ ብቃት አለ ወይ? ስትራቴጂው የሚፈልገው አመራር አለ ወይ? የተፈፃሚነት መመዘኛ ወሳኝ ነው። የተፈፃሚነትን መመዘኛ በሁለት አንኳር ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል - ሀ) አዋጪነት - ምን ያህል ዋጋ ያስከፍላል? ለ) አስተማማኝነት - ስትራቴጂው የሚፈልገውን ግብዓት (ሰው፣ አመራርና ድርጅት) መፍጠር ይቻላል?

ተቀባይነትን በተመለከተ ደግሞ ስትራቴጂው በዋና ዋና ባለድርሻ አካላት "ፍትህዊ ነው" ተብሎ ይታሰባል ወይ? ማኅበረሰቡ "መልካም" የሚለው ዓላማ "መልካም ባልሆነ" ስትራቴጂ ተግባራዊ ቢደረግ በዓላማውን መልካምነት ላይ ተጽዕኖ አለው? ለምሳሌ፣ አምባገነን አገዛዝን ኃላፊነት በሚሰማው አመራር መቀየር መልካም ነገር ነው። ይህ ሽግግር በሰላማዊ መንገድ ቢፈፀም እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ሆኖም ግን ይህ ሳይቻል ቀርቶ አምባገነኑ አገዛዝ በጉልበት ተቀይሮ ኃላፊነት የሚሠማው አመራር ሥልጣን ላይ ቢወጣ ሽግግሩ የተደረገበት መንገድ በአዲሱ አመራር ተቀባይነት ላይ ያለው ተጽዕኖ ምንድነው? "መልካም" የሆነው ዓላማ ከሞራል አንፃር ተመራጭ ባልሆነ ስትራቴጂ አማካይነት ተፈፃሚ ሆኖ መልካምነቱን እንደያዘ ማቆየት ይቻላል ወይ?።

ከላይ የተዘረዘሩት የስትራቴጂ አማራጮች በሙሉ የመጀመሪያውን የማጥሪያ ጥያቄ ማለፍ አለባቸው። የማጥሪያው ጥያቄ "ይህ ስትራቴጂ ወያኔን ማስወገድ ይችላልን" የሚል መሆን ይኖርበታል። ይሄንን ቁልፍ ጥያቄ በአዎንታ ያልመለሰ ስትራቴጂ ይሰረዛል። (ለመሰረዝ መቸኮል እንደሌለብን አስቀድመን ተናግረናል)። ይህንን መመዘኛ ያለፉ ስትራቴጂዎች ሁሉ በእነዚህ ሶስት መመዘኛዎች ሊለኩ ይችላሉ።

የዚህ ዘዴ አንዱ ጥቅምም <u>ሥርዓት ላለው ውይይት</u> የሚያዘጋጅ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ለባህላችን፣ ለአኗኗራችን ለታሪካችን ተስማሚ የሆነው ሰላማዊ ትግል ነው? ወይስ የትጥቅ ትግል? የሚለው ጥያቄ ብዙ የሚያወያይ ነው።

ሰላማዊና ህጋዊ ትግል እንደ ስትራቴጂ ተስፋ አለው ማለት <u>ህወሓት የሚቆጣጠረው ፓርላማ</u> ባወጣቸው ህጎች እየተገዙ፣ <u>ህወሓት የሚቆጣጠረው ፍርድ ቤት</u> የሚሰጠውን ውሳኔ እያከበሩ፣ <u>በህወሓት ፓሊስና ጦር ሠራዊት</u> ቁጥጥር ስር ተኩኖም ቢሆን <u>ህወሓት የሚቆጣጠረው የምርጫ ቦርድ</u> በሚያስተዳድረው ምርጫ <u>ራሱ ህወሓትን ማሸነፍ</u> ይቻላል ብሎ ማመን ነው። እኔ በበኩሌ ይኼ ተስፋ የሌለው ስትራቴጂ ነው ብዬ ስለማምን እሰርዘዋለሁ። የዚህኛው ስትራቴጂ መሰረዝ ደግሞ አራተኛውን ስትራቴጂ ማለትም "የትጥቅ ትግል እና ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ማቀላቀል" የሚለው ላይም የጥያቄ ምልክት ያስቀምጥበታል፤ ወይም ከአቢይ ስትራቴጂነት "በዚህ ስትራቴጂ ከሚያምኑ ድርጅቶች ጋር እንደምን ያለ የወዳጅነት ግኑኝነት ይኑረኝ? ወደሚል የሕዝብ ግኑኝነት ስትራቴጂነት ያወርደዋል።

የኔ እምነት ለሚጋራኝ የቀሩት ስትራቴጂዎች ሶስት ብቻ ናቸው። እያንዳንዱን ለየብቻ እያነሳን እንነጋገርባቸው።

ሰላማዊ ሆኖም ግን ህገወጥ ትግል እንደ ስትራቴጂ

ሰላማዊ ሆኖም ግን ህገወጥ ትግል እንደ ስትራቴጂ መውሰድ ማለት የአገዛዙን ህጎችንና ደንቦችን እየጣሱ "እምቢ አልገዛም" ብሎ በማመጽ ህወሓትን ከስልጣን ማስወገድ ይቻላል በሚል እሳቤ ላይ የተመረኮረዘ ነው። ይህ ስትራቴጂ ይበልጥ የሚታወቀው ሕዝባዊ እምቢተኝነት (Civic Disobiedence) በሚል መጠሪያ ነው። ከዚህ በኋላ እኔም "ሕዝባዊ እምቢተኝነት" የሚለውን መጠሪያ እጠቀማለሁ። በርካታ አምባገነን መንግሥታት በሕዝባዊ እምቢተኝነት መንኮታኮታቸው እውነት ነው። የቅርቦቹን ብቻ በምሳሌነት ብናነሳ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1980ዎቹ መጨረሻ የቀድሞ ሶቭየት ኅብረት ግዛቶች የነበሩ በኢስቶኒያ፣ ላትቪያና ሊቷንያ፤ በምሥራቅ አውሮፓ በፓላንድ፣ በቼክ ሪፑብሊክ፣ በስላቫኪያና በምሥራቅ ጀርመን፤ በእስያ በፊሊፒንስ እና በላቲን አሜሪካ ቮሊቪያ ውስጥ አምባገነን ሥርዓቶች ተንኮታኩተዋል። ከዚያም እአአ በ2003 ጽጌረዳማ አብዮት የሚል ስያሜ በአገኘው የጆርጂያ አብዮት፤ በ2005 "ብርቱካናማ አብዮት" የሚል ስያሜ የተሰጠው የዩክሬይን አብዮት፤ በ2005 "ሲዳር አብዮት" በተባለው የሊባኖስ አብዮት አገዛዞች ተቀይረዋል። ከዚያም በ2011 በቱኒዝያና በግብጽ "ጃዝሚን አብዮት" የተባለው ተካሂዶ የቤን ዓሊንና የሆስኒ ሙባረክ አገዛዞች ተወግደዋል። በመጨረሻም አምና በ2014 በቡርኪና ፋሶ በሁለት ቀናት አብዮት ከሃያ ዓመታት በላይ የተንሰራፋው አገዛዝ ተንኮታኩቷል። ከዚህ አጭር ዳሰሳ መረዳት እንደምንችለው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ውጤታማ የሆነባቸው የቅርብ ጊዜያት ምሳሌዎችም በሁሉም ከፍለዓለማት የሚገኙ መሆኑን ነው።

በአንፃሩ ደግሞ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ተሞክሮባቸው የከሸፉ ወይም በሕዝባዊ እምቢተኝነት ተጀምረው ወደ ትጥቅ ትግል የዞሩ ምሳሌዎችም አሉ። በሕዝባዊ እምቢተኝነት የቅርብ ጊዜ ምሳሌነት ሲወደስ የነበረው የዩክሬኑ ብርቱካናማ አብዮትም በየጊዜው እያመረቀዘ አገሪቷን ወደ መከፋፈል አድርሷት እስካሁንም መቋጫ አላገኘም። በ2011 በሊቢያ የተቀሰቀሰ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ወደ እርስ በርስ ጦርነት ተሸጋግሮ ኃያላን አገሮች ወደተሳተፉበት አውዳሚ ጦርነት ተሸጋግሯል። በሶሪያ የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ዓለምን አደጋ ላይ ወደ ጣለ የእርስ በርስ ጦርነት ዘቅጧል። በየመን የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ወደ እርስ በርስ ጦርነት ተሸጋግሮ አገሪቷን እያወደመ ከመሆኑም በላይ የአካባቢው አገሮች ሳይቀር ወደ ጦርነት እየሳበ ይገኛል።

ከላይ ለስትራቴጂዎች መመዘኛነት ያስቀመጥናቸው ሶስት መለኪያዎች፤ ተስማሚነት (Suitability)፣ ተፈፃሚነት (Feasibility) እና ተቀባይነት (Acceptability) አንፃር ሕዝባዊ እምቢተኝነት በምን ሁኔታዎች እንደሚሠራ በምን ሁኔታዎች ደግሞ እንደማይሠራ በማጥናት ከሀገራችን ተጨባጭ እውነታ ጋር ማገናዘብ ይጠበቅብናል። ይህ ሰፊ ምርምር የሚጠይቅ ሥራ በመሆኑ በዚህ ጽሁፍ የማይሞከር ነው። ሆኖም ዝርዝር ትንተና ውስጥ ሳንገባ ጠቅለል ያሉ ሀሳቦችን መስጠት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከታታይ በሆኑ አምባገነን ሥርዓቶች ሲበደል ቆይቷል። ቢያንስ በሶስት ተከታታይ ሥርዓቶች በመልካም አስተዳደር እና በልማት ስም ሲሸነገል ቆይቷል። ጥቂት ትላልቅ፤ በርካታ ትናንሽ አብዮቶች የከሸፉበት ሕዝብ ነው። ህወሓት በሰላማዊ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ቢቀየር ለውጡ የሚኖረው ተቀባይነት እና ከለውጡ በኋላ የሚመጣው መንግሥት የሚኖረው የሕዝብ ድጋፍ ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው። ምንም እንኳን ማስተማመኛ ባይኖርም በእንዲህ ዓይነት መንገድ የመጣ መንግሥት ወደ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር የሚያደርገው ሽግግር በአንፃራዊ መልኩ ቀና ይሆንለታል ብሎ ተስፋ ማድረግ ይቻላል። ተፈፃሚነትን በተመለከተ ግን ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነው። እስካሁን ከታዘብነው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ውጤታማ በሆነባቸው አገሮች ውስጥ የሚከተሉት ሶስት ነገሮች ተሟልተዋል። (1) በራስ መተማመንን ያጎለበተ ሕዝብ፣ (2) አንፃራዊ ነፃነት ያላቸው ተቋማት እና (3) በብልሃት የተቀመሩ የትግል ስልቶች። እነዚህ ሶስት ነገሮች በአገራችን ተሟልተዋልን (ወይም በአጭር ጊዜ ሊሟሉ ይችላሉን) ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ የሚያረካ አይሆንም።

ወደ ገጽ 19 ዞሯል

የትግል ስትራተጂ ... ከገፅ 18 የዞረ

በራስ መተማመንን በተመለከተ አገር ውስጥ የፓለቲካ ሥርዓትን ለመቀየር በመታገል ፋንታ እስከ ብር 100 000 አውጥቶ ሰሀራ በረሀን አቋርጦ በሊቢያ በኩል በላስቲክ ታንኳ ተሻግሮ አውሮፓ ለመድረስ የሚደረገው ጥረት፤ በእግር ሳይቀር ወደ ደቡብ አፍሪቃ የሚደረገው ጉዞ ብዛት እና ወደ መካከለኛ ምሥራቅ አገራት ለመሻገር ወደ የመን የሚደረገው አስፊሪ የሞት ጉዞ ኢትዮጵያዊያን በራሳችን ላይ ያለን የመተማመን መጠን መሸርሸሩን ያመለክታል። በህወሓት ላይ ተቃውሞ ለማሰማት ሳይቀር በውጭ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ድጋፍ መጠበቅ በአገር ውስጥ የነፃነትና መብት የማስከበር ትግል በገዛ ራሱ እግሮች እንዳይቆም አድርጎታል። በኢትዮጵያውያን ላይ የሰፈረው የፍርሀት ድባብ ከመወፈሩ የተነሳ በማኅበረሰባችን ውስጥ የእርስ በርስ መተማመን እየጠፋ ነው። ለወትሮው በጓዳዊ መተሳሰብ ይታወቁ የነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ በጋራ ከመቆም ይልቅ በዘር ተቧድነው ሲቆራቆሱ ማስተዋል ልብን ይሰብራል። እርግጥ ነው የህወሓት ፋሽስቶችን የጭካሬ እርምጃ እየተጋፈጡ ያሉ ወጣቶች አሉ፤ ሆኖም ባለፉት 25 ዓመታት ወያኔ በልበሙሉነት፣ በአልደፈር ባይነት፣ በነፃነትን ናፋቂነት እሴቶቻችን ባደረሰው ውድመት ሳቢያ አዳክሞናል። በራስ መተማመን ሳይጎለብት አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት ከባድ ነው።

አንፃራዊ ነፃነት ያላቸው ተቋማት ጉዳይ። በሕዝባዊ እምቢተኝነት አምባገነን አገዛዞች በተገረሰሱባቸው አገሮች ሁሉ የተወሰኑ ተቋማት አንፃራዊ ነፃነት ነበራቸው። ለምሳሌ በፓላንድና በቼክ ሪፑብሊክ የለውጡ ዋነኛ አራማጆች የሙያ ማኅበራት ነበሩ። እነዚህ የሙያ ማኅበራት አንፃራዊ ነፃነት ነበራቸው። በፓላንድ ከሠራተኛ ማኅበር በተጨማሪ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለነፃነት ትግል ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክታለች። በዩክሬንና በጆርጂያ ፓርላማዎች አንፃራዊ ነፃነት የነበራቸው በመሆኑ የሕዝቡን ትግል የሚደግፉ የፓርላማ አባላት ነበሩ። ዩክሬን ውስጥ የሕዝቡን ትግል በመደገፍ የተወሰኑ የፓርላማ አባላት ፓርላማው ውስጥ የረዘበ አድማ አድርገዋል። ጥቂት ቆይቶም አብላጫው የፓርላማ አባላት የትግሉ ደጋፊዎች ሆኑ። በቱኒዝያ፣ ግብፅና ቡርኪና ፋሶ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ሊሳካ የቻለው በኃላፊነት ስሜት የሚንቀሳቀስ አንፃራዊ ነፃነት ያለው የጦር ሠራዊት ስለነበራቸው ነው። በሶስቱም አገራት ጦር ሠራዊቱ የሕዝቡን ጥያቄ በሚያስታግስ መልኩ ተንቀሳቅሷል። በብዙዎቹ አገራት የፍትህ፣ የሚዲያ እና የአካዳሚያ ተቋማት አንፃራዊ ነፃነት ነበራቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው። አገራችን ኢትዮጵያ ትንሽ እንኳን የነፃነት ሽውታ ያለበት አንድም ተቋም የላትም። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፣ የፍትህ አካላቱ፣ ሚዲያው፣ አካዴሚያው በአገዛዙ ከመታፈናቸው በተጨማሪ ዘረኛ በሆነ መንገድ በመደራጀታቸው አገራዊ እይታ እንዳይኖራቸው ተደርጓል። ሲቪል ማኅበራት ፈጽሞ እንዳይኖሩ ተደርጓል፤ ። የሃይማኖት ተቋማት ሳይቀሩ የሥርዓቱ ተቀጥላ ተደርገዋል። ወያኔ በሲቪል ማኅበራት ላይ የዘመተው እንደማኅበረሰብ የመዝለቃችን ዋስትና የሆነው ማኅበራዊ ካፒታላችንን ለማጥፋት ነው። እናም ጉዳቱ የማኅበራቱ ተግባር መሰናከሉ ብቻ ሳይሆን በአባላቱ መካከል ሊዳብር ይችል የነበረዉ የመተማመን መጠን መጥፋቱም ጭምር ነው።። ማኅበራዊ ካፒታልን ማውደም ግዑዝ ካፒታል (ለምሳሌ ድልድይን) ከማፍረስ እጅግ የባሰ ጉዳት ያስከትላል።።

በብልሃት የተቀመሩ ስትራቴጂዎችና ስልቶችን እጥረት በሚመለከት ለጊዜው የማነሳው ጉዳይ የለም።

ሕዝባዊ እምቢተኝነትን ውጤታማ ያደርጋሉ ከሚባሉ ሶስት መሠረታዊ ነገሮች (በራስ መተማመንን ያጎለበተ ሕዝብ፣ አንፃራዊ ነፃነት ያላቸው ተቋማት እና በብልሃት የተቀመሩ የትግል ስልቶች) ሁለቱ አለመሟላታቸው ብቻ ሳይሆን በአነስተኛ ደረጃ ላይ እንኳን አሉ ማለት አይቻልም። ይህ ግምገማ ትክክል ከሆነ አሁን ባለው ሁኔታ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ብቻውን እንደ ስትራቴጂ በዛሬይቷ ኢትዮጵያ ተግባራዊ መሆን የሚችል (feasible) ስትራተጂ አይደለም። ስትራቴጂው ተስማሚ ቢሆንም ግብዓቶች ይጎሉታል።

ተቀባይነትን በተመለከተም ሕዝባዊ እምቢተኝነት እንደስትራቴጂ ተቀባይነት እንዲያገኝ ብዙ መሠራት አለበት። ኢትዮጵያ ውስጥ "መንግሥት ለመሆን የሚፈልግ በመንግሥት ላይ ሸፍቶ ተዋግቶ አሸንፎ ይንገስ፤ አለበለዚያ ለነገሠው በታማኝነት ይገብር" የሚል ያልተፃፈ ህግ ያለ ይመስላል። በዚህም ምክንያት ሳይሸፈት መንግሥት ላይ ማመጽ ለኢትዮጵያዊያን የሚገባ ነገር አይደለም። ወይ መሸፈት፤ አለያም መገዛት ነው። በዚህም ምክንያት ሕዝባዊ እምቢተኝነት እንደ ስትራቴጂ እምብዛም ተቀባይነት የለውም። ይህ ስሜት ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊቀየር የሚችል ይመስለኛል፤ ሆኖም ግን ብርቱ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ይፈልጋል።

ትጥቅ ትግል እንደ ስትራቴጂ

በአገራችን ታሪክ ውስጥ ጠመንጃና ስልጣን ከፍተኛ ቁርኝት አላቸው። አብዛኛዎቹ የስልጣን ሽግግሮች የተደረጉት በጠመንጃ ታግዘው ነው። ጦረኝነት ኢትዮጵያዊ ባህል ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠመንጃንና ባለጠመንጃን ያወድሳል። ስለዚህም ትጥቅ ትግል እንደ ስትራቴጂ ምናልባት በልሂቃኑ ዘንድ ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይን የተቀባይነት ችግር የለበትም። ተፈፃሚነትን በሚመለከት ደግሞ ወያኔ በትጥቅ ትግል የማይሸነፍበት ምክንያት የለም። ወያኔ የኃላያን አገሮች ድጋፍ ያለው መሆኑ፤ ጦሩን በዘረኛ መንገድ ማዋቀሩ እና በአለም ፓለቲካ የሽብርተኝነት ስጋት መኖሩ በትጥቅ የሚታገዙ የነፃነት ትግሎች የሚጠብቃቸው ተግዳሮት ቀድሞ ከሚታወቀው በላይ እንዲሆን አድርገዋል። ይህ ትግሉን ያከብደዋል እንጂ ወያኔ በጉልበት የማይሸነፍ ኃይል እንዲሆን አያደርገውም። ተስማሚነትን በሚመለከት ግን ሁኔታው ለየት ይላል። "በጠመንጃ ወደ ስልጣን የመጣ ኃይል አገሪቱን ወደ ዲሞክራሲ ሊመራ ይቻላል ወይ?" የሚለው ጥያቄ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም። በዓለም ታሪክ ውስጥ በጠመንጃ ወደ ስልጣን መጥተው ወደ ሲቪል አስተዳደር (በአንዳንድ ሁኔታዎችም ወደ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር) የተሸጋገሩ ሥርዓቶች አሉ። ኮሎምቢያ በ1957፣ ቬንዙዌላ 1958፣ ቦሊቪያ 1997ን፤ ስፔን 1931፣ ቱርክ 1960፣ ፓርቹጋል 1974፣ ጋና 1979፣ በቅርቡ በ2014 ግብጽን (ከመሀመድ ሙርሲ በኃላ የአብዱል ፈታ ኤል ሲሲ በመንፈንቅለ መንግሥት መምጣት) እና ሌሎች በርካታ ምሳሌዎችን በመዘርዘር መከራከር ይቻላል። ታሪክ፣ ዜጎችን ፈጅተው የመጡ አምባገነኖች ወደ ሲቪል አስተዳደር ሲቀየሩ አይታለች፤ በአንፃሩ ደግሞ በሰላማዊ መንገድ በሕዝብ ይሁንታ ወደ ስልጣን መንበር ወጥተው አስከፊ አምባገነን የወጣቸውን ታውቃለች። በክፋቱ የሚታወቀው የሂትለር ናዚ መንግሥት ወደ ስልጣን የመጣው በምርጫ ነው፤ ስታሊንም ሌኒንን ተክቶ እንጂ ገልብጦ የመጣ አይደለም። በሰላማዊ መንገድ የመጣ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ መሆኑን ማረጋገጥ እንደማይቻል ሁሉ በጠመንጃ የመጣ ሁሉ አምባገነን ይሆናል ብሎ ማጠቃለል አይቻልም። ይልቅ ወሳኙ ነገር ለውጡ በመጣበት ወቅት ያለው የኃይል ሚዛንና የጠንካራ ተቋማት መኖር ወይም አለመኖር ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የዲሞክራሲ ተቋማት ይቅሩና አገራዊ ተቋማት እንኳን የሉም። አገራችንን እንደ አገር ሰብስበው የያዟት ተቋማት እየተዳከሙ ናቸው። ከአገራዊ ስሜት ጋር የሚፎካከር አካባቢያዊ ስሜት ፋፍቷል። ህወሓት በስልጣኑ ለመቆየት ሲል አጎራባች ማኅበረሰቦችን በብሔር ስም፤ የተለያዩ ሃይማኖት አማኞችን በአከራሪነት ስም ሲያጋጭ የቆየ በመሆኑ የትጥቅ ትግል ከቁጥጥር ካፈተለከ የት ሊያደርስ እንደሚችል መገመት ያስፈራል። በዚህም ምክንያት የትጥቅ ትግል እንደ ስትራቴጂ ተፈፃሚ እና ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ተስማሚነቱ አጠራጣሪ ነው።

ትጥቅ ትግል እና ሰላማዊ ሆኖም ግን ህገወጥ ትግል ተቀላቅሎ እንደ ስትራቴጂ

ሕዝባዊ እምቢተኝነትም ሆነ የትጥቅ ትግል ለየብቻቸው በስትራቴጂነት ሲቀርቡ የሚጎላቸው ነገር አለ። ግባችን ወያኔን ማስወገድ ብቻ አይደለም፤ ከወያኔ በኋላ የምትኖረን ኢትዮጵያ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት እና አገራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ እንዲሆን እሻለሁ። የምንፈልገው የትግል ስትራቴጂ ወደዚህ የሚያደርሰን መሆን ይኖርበታል። አሁን ባለው ሁኔታ ሕዝባዊ እምቢተኝነትም ሆነ የትጥቅ ትግል ለየብቻቸው ወደዚህ ግብ ሊያደርሱን ይችላሉ የሚል እምነት የለኝም።

ሕዝባዊ እምቢተኝነት ወደምንፈልገው ግብ ሊያደርሰን አይችልም ያልኩባቸው ሁለት ዋነኛ ምክንያቶች ከላይ ተዘርዝረዋል። ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የዘራው ሽብር እና የዘረጋው የስለላ መረብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞውን በአደባባይ እንዳይገልጽ አድርጎታል። ፍርሀትን አሸንፎ የስለላን መረብ በጣጥሶ የሚወጣ ሕዝብ ያስፈልጋል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነት የሚደራጅበት ሁኔታ ባለመኖሩ የተደራጀ ሰላማዊ ትግል ማድረግ አልተቻለም። በዚህ ረገድ የተሻለ ሥራ እየተሠራ ያለው በሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ሲሆን ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያንን ወደዚያ ደረጃ ማድረስ መቻሉ አጠራጣሪ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የመብት ጥያቄዎች ሀይማኖታዊ ወይም ክልላዊ ብቻ ሆነው እንዳይቀሩ፤ የመብት ጥያቄዎች በቂ ምላሽ የሚያገኙት የፓለቲካ ሥርዓቱ ሲለወጥ እና ዲሞክራሲያዊ አመራር ሲሰፍን እንደሆነ ሰፊ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት በኢትዮጵያዊያን የተገነባ ነገር ግን በህወሓት የሚመራ ነው። ሠራዊቱ አመራሩን አስወግዶ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆም የሚረዳው አካል ያስፈልጋል። እነዚህን ወሳኝ ተግባራት ለመከወን ነው የታጠቀ ሕዝባዊ ኃይል የመኖሩ አስፈላጊነት ጎልቶ የሚወጣው።

"ትጥቅ ትግል እና ሰላማዊ ሆኖም ግን ህገወጥ ትግል ተቀላቅሎ እንደ ስትራቴጂ" ተብሎ የተገለፀው በአጭሩ "ሁለገብ የትግል ስትራቴጂ" የሚባለው ነው። ሁለገብ የትግል ስትራቴጂ ሕዝባዊ እምቢተኝነትና የትጥቅ ትግል (ሕዝባዊ አመጽ) ተደጋግፈው እንዲሄዱ የሚያደርግ ስትራቴጂ ነው። ነፃና አገራዊ ተቋማት ባለመኖራቸው ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት በመሙላት ረገድ እና ወያኔ በሕዝብ ላይ ያሰፈነውን ፍርሀት ለመግፈፍ የታጠቀ ሕዝባዊ ኃይል ከፍተኛ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። የሕዝባዊ እምቢተኝነት መኖር ሕዝብ የትግሉ ባለቤት እንዲሆን ያደርገዋል። "ሁለገብ ትግልን" ስትራቴጂ አድርገን ከወሰድን "ሕዝባዊ እምቢተኝነት" እና "ሕዝባዊ አመጽ" ወደ ስልትነት ይወርዳሉ። ይህ ማለት ወደተፈለገው ግብ የሚደረሰው ስትራቴጂው በሙሉ በተግባር ላይ ሲውል ነው እንጂ አንዱ ብቻውን ተግባራዊ ሲሆን አይደለም ማለት ነው። በሁለገብ የትግል ስትራቴጂ ላይ የሚቀርቡ ሁለት ዓይነተኛ ትችቶች አሉ። አንዱ የአመጽ ትግልን እና ሰላማዊ ትግልን ማደባለቅ አይቻልም፤ "ውሀና ዘይት" ናቸው የሚል ነው። እርግጥ ሁለቱ በሚፈልጉት የሰው ዓይነትም ሆነ አደረጃጀት የተለያዩ ናቸው። ይህ ማለት ግን እያንዳንዳቸው በየሚፈልጉት አደረጃጀት ተደራጅተው ሊደጋገፉ አይችሉም ማለት አይደለም። በመሠረቱ እስካሁን የሚታወቁ የነፃነት ትግሎች እና አብዮቶች ሁሉ ምጣኔዎቸው ይለያይ እንጂ የሕዝባዊ እምቢተኝነትና የሕዝባዊ አመጽ ድብልቆች ናቸው። ደቡብ አፍሪቃን ከአፓርታይድ ነፃ ያወጣው ትግል ሁለቱ ስልቶች ተደጋግፈውበታል። በምሥራቅ አውሮፓና በሰሜን አፍሪቃ የተካሄዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎችም ቢሆኑ አመጽና እምቢተኝነት የተደባለቀባቸው አሊያም የተፈራረቁባቸው ነበሩ። እንዲያዉም ዛሬ ያለውን የሰሜን አፍሪቃና መካከለኛ ምሥራቅ ሁኔታ ስናጤን ለማስተዋል ከምንገደዳቸው መራር ሀቆች አንዱ በሕዝባዊ እምቢተኝነት አምባገነን አገዛዞች ተገርስሰው በምትካቸው ደካማ መንግሥታት ወደስልጣን ከመጡ

ወደ ገጽ 20 ዞሯል

ከገፅ 19 የዞረ

የተራዘመ ቀውስ ሊከተል የሚችል መሆኑ ነው። ይህ እውነታ ከመጀመሪያው የተደራጀ ሕዝባዊ ኃይል መኖር አስፈላጊነትን ያጎላዋል።

ሁለተኛው ትችት ደግሞ የትጥቅ ትግል መኖር አምባገነኖች ወታደራዊ ኃይላቸውን እንዲጠቀሙ መንገድ ይከፍትላቸዋል በውጤቱም የበርካታ ሕዝብ ሕይወት አደጋ ላይ ይወድቃል የሚል ነው። ሁለገብ ትግል እንደትግል ስትራቴጂ በአማራጭነት የሚወሰድባቸው አገሮች ውስጥ ያሉ መንግሥታት ሠራዊታቸውን በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ከማዝመት የማይመለሱ እንደ ህወሓት ዓይነት ያሉ አገዛዞች ናቸው። እነዚህ አገዛዞች የበዛ ጥፋት የሚያደርሱት ራሱን መከላከል የማይችል ሆኖም ግን ጠንከሮ የሚታገል ተቃዋሚ ሲገጥማቸው ነው። እንደዚህ ዓይነት አገዛዞች በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ከመተኮስ የማይመለሱ በመሆናቸው በመለሳለስ ኪሳራ ማስቀነስ አይቻልም። በመሠረቱ እኛም አገር ቢሆን ሰላማዊ ትግልና የአመጽ ትግል የሚያስከፍሉት ዋጋ መሳ ለመሳ ሆኗል።

እዚህ ላይ "ሁለገብ ትግል" ራሱ የብዙ ስትራቴጂዎች ጥቅል ስያሜ መሆኑ ማስታወስ ይበጃል። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች "ክብሪቱን አንዴ ለኩሉልን እንጂ ከዛ ቀጥሎ ያለውን ለኛ ተውልን ይላሉ" ይህ አነገጋር ወደ ስትራቴጂ ሲመነዘር የሚከተውን ይመስላል። ህወሓት ከስልጣን የሚወገደው ሕዝባዊ አመጽና ሕዝባዊ እምቢተኝነት በፈረቃ በተግባር ላይ በሚወሉበት ሁለገብ ትግል ነው። የፈረቃው ቅደም ተከተልም በመጀመሪያ ሕዝባዊ ኃይል ወታደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ በዚህ የተደፋፈረው ሕዝብ በሥርዓቱ ላይ በማመጽ ወያኔን ያስወግዳል፤ ጊዜዓዊ የሽግግር መንግሥትም ይቋቋማል። ሌሎች ሰዎች ደግሞ "እናንተ ከዳር እኛ ከውስጥ እናጣድፈዋለን" ይላሉ። ይህ አባባል ወደ ስትራቴጂ ሲመነዘር የሚከተለውን ይመስላል። ህወሓት ከስልጣን የሚወገደው ሕዝባዊ አመጽና ሕዝባዊ እምቢተኝነት በአንድነት በተግባር ላይ በሚወሉበት ሁለገብ ትግል ነው፤ ዳር አገር ትጥቅ ትግል መሀል አገር ደግሞ ሕዝባዊ እምቢተኝነት፤ ሁለቱን ተደጋግፈው ወያኔን ያስወግዳሉ፤ ጊዜዓዊ የሽግግር መንግሥትም ይቋቋማል። እንዲህ እያልን ከሁለገብ ትግል ብዙ አማራጭ ስትራቴጂዎችን ማሰብ እንችላለን። ከዚህም ሌላ ምን ያህል አመጽ ምን ያህሉስ እንቢተኝነት መደባለቅ ይኖርበታል የሚለው ራሱ ቁጥር ስፍር የሌላቸው አማራጮችን ይዞ የሚመጣ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው የትግል ስትራቴጂ መረጣ የአንድ ወቅት ሥራ የማይሆነው አዕምሮዓችን በአሠራን መጠን አማራጮችን እያሰፋን የምንመጣ በመሆኑም ጭምር ነው።

ማጠቃለያ

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ "የትግል ስትራቴጂ" እና "የትግል ስትራቴጂ መረጣ" ሲባል እኔ የምረዳውን ለማካፈል ሞክሬዓለሁ። "ሁለገብ ትግል" እንደ ትግል ስትራቴጂ ምን ማለት እንደሆነ እና ለምንስ ለኢትዮጵያ ተመራጭ ነው ብዬ እንደማምን የግሌን አስተያየት አቅርቤዓለሁ። ይህ ጽሁፍ ሁለገብ ትግል ለኢትዮጵያ ይበጃል የምንል ሰዎች ቢያንስ ሳናስብበትና ሳንጨነቅበት በግልብ የወሰነው ጉዳይ አለመሆኑ ያስረዳል ብዬ አደርጋለሁ።

አስተያየት መስጠት ለምትፈልጉ: tkersmo@gmail.com

ልዩ ካፌ Liyu Café

301-585-1717

8395 Colesville Road E
Silver Spring, MD

ከሲልቨር ስፕሪንግ ሜትሮ ስቴሽን
አጠገብ ሌኖክስ አፓርትመንት ህንጻ ስር